የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**FOR IMMEDIATE RELEASE**

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) licenses the first securities exchange.

Addis Ababa, Ethiopia – 7/12/2024

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) is pleased to make a historic announcement of the licensing of the Ethiopian Securities Exchange S.C (ESX), marking a monumental step in Ethiopia's capital market development. This significant milestone is part of the broader macroeconomic reform agenda initiated five years ago to build a modern, well-regulated capital market that supports sustainable economic growth.

Speaking on this occasion, **Ms. Hana Tehelku**, Director General of ECMA, stated, "The licensing of our first securities exchange marks a transformative milestone in our journey to establish a vibrant capital market. This achievement signifies the foundation of a robust capital market, enabling businesses to access sustainable financing and providing investors with new opportunities to grow their wealth. As a regulator, we are committed to fostering transparency, integrity, and innovation to ensure this market thrives and contributes to our shared vision of economic prosperity."

ECMA has also granted the Ethiopian Securities Exchange an OTC (Over-The-Counter) market license, allowing the ESX to be a platform where companies that do not meet the listing requirements of the main market segment can trade their shares, fostering a more inclusive and accessible capital market.

Now, the Ethiopian Securities Exchange Share Company is the sole entity licensed to operate the platform for securities trading in Ethiopia. The public is advised that shares and other securities offered to the public may only be traded through a licensed exchange.

**About ECMA**

The Ethiopian Capital Market Authority (ECMA) stands as a pivotal institution mandated to foster the development and regulation of the capital market within the Federal Democratic Republic of Ethiopia. Established under Article 3(1) of the Proclamation, the ECMA operates as an independent regulatory body with its own juridical identity, reporting directly to the Prime Minister of Ethiopia. Embracing a multifaceted approach, the ECMA is committed to enhancing investor confidence, facilitating capital mobilization, and promoting sustainable economic growth through robust regulatory frameworks and strategic initiatives.
For more information, please visit ecma.gov.et.

**For enquiries & additional information contact**
Saron Woldegabriel
Director, Communications & Public Relations
Phone: 011-5-57-81-62
Email: swoldegabriel@ecma.gov.et

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**ጋዜጣዊ መግለጫ**

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለንዋዮች ገበያ ፈቃድ ሰጠ።

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ- 29/3/2017

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለየኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አክሲዮን ማህበር ፈቃድ መስጠቱን በደስታ ያሳውቃል። የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በመንግስትና የግል ዘርፉ ትብብር በአክሲዮን ኩባንያነት እንደሚቋቋምና አስፈላጊ መስፈርቶችን ሲያሟላ በባለስልጣኑ ፈቃድ እንደሚሰጠው በካፒታል ገበያ አዋጁ የተገለጸ ሲሆን በዚሁ አግባብ የተመሰረተው የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለንዋዮች ገበያ አክሲዮን ማህበር አስፈላጊ መስፈርቶችን በማሟላት ሰነደ ሙዓለንዋዮችን ለማገበያየት ዝግጁ መሆኑ በመረጋገጡ ባለስልጣኑ ስራ መጀመር የሚያስችለውን ፈቃድ ሰጥቶታል።

የሰነደ ሙዓለንዋዮች ገበያው ፈቃድ በማግኘት ስራ ለመጀመር ዝግጁ መሆን ከአምስት አመት በፊት የተጀመረው የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም አንድ አካል የሆነው በሀገራችን ቁጥጥር የሚደረግበት ዘመናዊ የካፒታል ገበያ የመመስረት ሂደት የመጨረሻው ደረጃ ላይ መደረሱን የሚያረጋግጥ ነው።

የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለንዋዮች ገበያ ሰነደሙዓለንዋዮችን ግልጽ በሆነና በተቀላጠፈ መንገድ ማገበያየት የሚያስችል ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ስርዓት የዘረጋ ሲሆን ገበያው ስራ ሲጀምር ህብረተሰቡ የኩባንያዎችን አክሲዮኖችን ጨምሮ ለህዝብ ሽያጭ የቀረቡ ሌሎች ሰነደ ሙዓለንዋዮችን በቀላሉ መሸጥና መግዛት የሚችልበትን እድል ይፈጥራል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሀና ተኸልቁ እንዳሉት የመጀመሪያውን የሰነደ ሙዓለንዋይ ገበያ ፈቃድ መስጠታችን ዘመናዊ የካፒታል ገበያ ለመፍጠር በሚደረገው ሂደት ወሳኝ ምዕራፍ ሊባል የሚችል ነው። ገበያው ዘላቂ የፋይናንስ አቅርቦት ለሚፈልጉ ተቋማት እንዲሁም ለህብረተሰቡ አማራጭ የኢንቨስትመንት እድል የሚሰጥ ነው። ገበያውን እንደሚቆጣጠር ተቋም የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ይህ ገበያ ግልጽ፣ ውጤታማና ተዓማኒ ገበያ እንዲሆንና ለጋራ የኢኮኖሚ ብልጽግና ጉልህ ሚና እንዲጫወት ለማስቻል አስፈላጊውን ስራ በሙሉ በቁርጠኝነት እንደሚሰራ ያረጋግጣል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለንዋዮች ገበያ አ/ማህበር ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ የተሰጠው ሲሆን ይህም በዋናው የገበያው መድረክ ላይ ለመገበያየት የሚያስፈልገውን መመዘኛ ማሟላት ያልቻሉ ኩባንያዎች በገበያው እንዲሳተፉ በማድረግ ገበያው ሁሉንም ማሳተፍ የሚችል አካታች እንዲሆን ያስችላል።

ባለስልጣኑ የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አክሲዮን ማህበር በኢትዮጵያ ውስጥ የሰነደ ሙዓለንዋዮችን ግብይትን ለማከናወን ፈቃድ የተሰጠው ብቸኛው ድርጅት መሆኑን እየገለጸ ለህዝብ ሽያጭ የቀረቡ አክሲዮኖችና ሌሎች ሰነደ ሙዓለንዋዮችን መገበያየት የሚቻለው በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ፍቃድ ከተሰጠው ገበያ ብቻ መሆኑን ያሳውቃል።

**ስለ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን**

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያን ለማሳደግ እና ቁጥጥር እንዲያደርግ የተቋቋመ ሲሆን በካፒታል ገበያ አዋጁ አንቀፅ 3(1) መሰረት ባለስልጣኑ ህጋዊ ሰውነት ያለው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪ የሆነ ተቆጣጣሪ ተቋም ነው። ባለስልጣን መ/ቤቱ ኢንቨስተሮች የመጠበቅ፣ የገበያውን ተዐማኒነት የማረጋገጥ ፣ ስርዐታዊ ስጋቶችን የመቀነስ እና ገበያውን የማሳደግ አላማን በማንገብ በጠንካራ የቁጥጥር ማዕቀፎች እና ስልታዊ ስትራተጂዎች እየሰራ የሚገኝ ተቋም ነው።

ለበለጠ መረጃ ድረገጻችንን ይጎብኙ ecma.gov.et

**ለጥያቄዎች እና ለተጨማሪ መረጃ**

ሳሮን ወ/ገብርኤል
የኮምኒኬሽን እና ህዝብ ግኑኙነት ዳይሬክተር
የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን
ስልክ- 011-5-57-81-62
ኢሜል- swoldegabrie@ecma.gov.et